# Union of Tigrians in Europe
## Board of Directors
## ማሕበር ተጋሩ ኣውሮፓ

uteboard@gmail.com

ዕለት ፤ 21 ዲሰምበር ፣ 2017
ቍፅሪ ፤ ማተኣወ 20171221/1

**የሐዘን መግለጫ**

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሃገራችን እየተስተዋለ ያለው አለመረጋጋት በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በሚፈጠሩ ፀቦች ፣ በእግርኳስ ደጋፊዎች መካከል በሚታዩ እልኾች እና ሌሎች የተለያዩ መንስኤዎች ጋር ታጋምዶ ነው ። ችግር ሲኖር ነገሩን በሰላማዊ መንገድ እንደመፍታት ያልነበረና አሳፋሪ የዘር ስም እየሰጡ መቧደን ከተስተዋለ ሰንበትበት ብሏል ። ምንም መነሻ ይኑረው ምን አንድም ኢትዮጵያዊ በብሄሩ ምክንያት መሞት የለበትም ። ስሕተት የሚታረመውም በመገደዳደል ሊሆን አይችልም አይገባምም ።

ሰሞኑን በሃገራችን በተለያዩ አከባቢዎች የተከሰቱት ግጭቶች ደግሞ ይባስ ብለው መልካቸውን ቀይረው የለየላቸው የጅምላ ጭፍጨፋ ወደ መሆን ተሸጋግረዋል ። ይኽ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ አሳዛኝም አስደንጋጭም ነው ። በነዚህ አስደንጋጭ ጊዜያት ለሞቱት ዘላለማዊ ዕረፍትን ፣ለወዳጅ ዘመዶቻቸውና ለመላው ኢትዮጵያውያንም መፅናናትን እንመኛለን ።

ማሕበራችን ባሉት አደረጃጀቶች ተከታታይ ሃገራዊና አህጉራዊ ውይይቶች በማድረግ አለን በምንለውና በምንመካበት ኢትዮጵያዊ የፍቅር እና የመተሳሰብ እሴት ላይ ውይይቶችን ያካሂዳል ፣ ኢትጵያውያን ከሆኑ ሁሉም የተጋረጠብንን አደጋ የምንቀለብስበትን መንገድ ላይም ይመክራል ። አገር አፍርሶ መልካም አስተዳደርን መመኘት አይቻልምና አገራችን ከተጋረጠባት አደጋ ማዳን የሁሉም ኢትዮጵያውያን ይደር የማይባል የቤት ሥራ ነው ብለንም እናምናለን ።

የዘር ግጭት አስነዋሪና ኋላቀር ከመሆኑም በላይ በተለይ የመቻቻል ተምሳሌት የሆነውን ኢትዮጵያውያንን በፍፁም አይገልፀንም ። ኢትዮጵያውያን እንዳባቶቻችን በሃይማኖትና በዘር ሳንለያይ የውጭ ወራሪን ስንመክት ነው የሚያምርብን ፣ ሃገር ሲባል አንድነት ነው የሚገልፀንና እንደሃገር ተከብረን እንድንቀጥል የሚያደርገንና እስካሁንም ያቆየን ።

ስለዚህ ማንም ይሁን ምን ለሰላም ቅድሚያ እንዲሰጥ ፣ መንግሥትም የዜጎችን ደኅንነት የመጠበቅ ሐላፊነቱን እንዲወጣ ፣ በዚህ አሳዛኝና ኋላቀር ድርጊት ተሳታፊ የሆኑት አካላት ላይም ሕጋዊ እርምጃ እንዲወስድና ውጤቱም በይፋ ለሕዝብ እንዲያሳውቅ እናሳስባለን ።

ሰላም ለሃገራችን ኢትዮጵያ እና ሕዝቦችዋ !

ማሕበር ተጋሩ ኣውሮፓ (በአውሮፓ የትግራይ ተወላጆች ማሕበር)

ታኅሳስ 12 ፣ 2010 ዓም